# ውድ ሀገር ኢትዮጵያ በጨካኘፊ መናፍቅ ዜጋዋ የዘፈን ድርሰት ስትገለጽና ስትጠቃ!

ከሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

•

ሥነ ኪን በዘልማድ (ሥነ ጥበብ) የአንድን ሀገር ገጽታና የሕዝቧን ሰብእና አስተሳሰብ ማንነት ባሕል ወግ ወዘተረፈ። ለመቅረጽ ለመገንባት ዐቢዩን ሚና ይጫወታል፡፡ እግዚአብሔር ይመስገንና ሀገራችን ኢትዮጵያ በእኛ ከያኔያን ብቻ ሳይሆን እንደነ ሆሜር ሄሮዱቶስ ወልፍራም በመሳሰሉት ምዕራባዊያን ጸሐፍት ከያኔያን በሥነ ኪን ከማንም ሀገር በላይ ተገልጻለች፣ ተወድሳለች፣ ተንቆለጳጵሳለች፣ ገናለች፣ ከብራለች፡፡ ይህ የመከበር የመወደስ ከፍ ከፍ የማለት ጸጋዋ ከጸሐፍት ከያኔያንና ሥራዎቻቸው አልፎም በታላቁ መጽሐፍም (በመጽሐፍ ቅዱስም) ከፍ ያለ ቦታ አሰጥቷት ይገኛል፡፡

ይሄንን ጽሑፍ ለመጻፍ ምክንያት የሆነኝ ባለፈው ሰሞን የአንድ ዳንኤል አድማሱ (ዳን አድማሱ) የተባለ ዘፋኝ የዘፈን ጥራዝ (የሙዚቃ አልበም) ገበያ ላይ ውሎ ለገበያ ያበቁቱ (ፕሮዱዩሰሮቹ) ይሄንን የዘፈን ሥራ በተለያዩ የሬዲዮ (የነጋሪተ ወግ) "የመዝናኛ" ዝግጅቶች ዘፋኙ እንዲቀርብ እያደረጉ ለሕዝብ ለማስተዋወቅ ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት በእነዚህ የመዝናኛ ዝግጅቶች ተደጋግሞ የተነሣ አንድ ስለ ኢትዮጵያ የተዘፈነ የዘፈን ጭብጥ በጣም አስከፋኝና ነው ይሄንን ጽሑፍ ለመጻፍ የተገደድኩት፡፡

የዘፈኑ ጸሐፊ ኤልያስ መልካ የተባለ የዘፈን አቀናባሪ ነው፡፡ ይሄ ልጅ በጣም አበሳጭቶኝ እንደ ሌሎቹ ሥራዎቹ ልለፈው ብየ እንዳለፍኩት ሁሉ ልልፈው ሳልል እንድተቸው ሲያደርገኝ ይሄ ለሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡

ከዚህ ቀደምም ለኢዮብ መኮንን በጻፈለት "የቋንቋ ፈላስፋ" በሚለው ዘፈኑ በምዕራቡ ዓለም እንደምናየው ሁሉ ትዕይንተ ወግ (የቶክ ሾው) ለአንድ ሀገርና ማኅበረሰብ ሥልጣኔ ንቃተ ኅሊናና የተቃና የተረጋጋ ማኅበራዊ ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) መስተጋብር ያለውንና የሚያበረክተውን የላቀ ፋይዳ ጨርሶ ባለመገንዘብ እኛም በዚህ መድረክ ሐሳባችንን እያንሸራሸርን ችግሮቻችንን እየተወያየን እየገለጽን እየመከርን፣ እያነሣን፣ መላ መፍትሔ እየተጠቋቆምንበት፣ የመናገር መብታችን ተግባራዊ እያደረግንበት ተጠቃሚ ልንሆን የምንችልበትን የትዕይንተ ወግ (የቶክ ሾው) መድረኮችን አላስፈላጊ መሆናቸውን አምኖ "የቋንቋ ፈላስፋ" የሚለውን ዘፈን በመጻፍ በወቅቱ የነበረውን "ሐምሳ ሎሚ" የተባለ የትዕይንተ ወግ ዝግጅት ሥያሜውን በዘፈኑ ስንኞች በማንሣት ጭምር የትዕይንተ ወግ መድረኮቹ እርባናና ጠቀሜታ የሌላቸው እንደሆኑ በመግለጽ በይነ ሕዝብ (ዴሞክራሲ) በሰፈነባቸው ሀገራት የማይተካ ሚና እየተጫወቱ በርካታ ጥቅም ያበረከተላቸውን ይህን ተሞክሮ በእኛም ሀገር ቢለመድ በሁሉም ረገድ ታላቅ ጠቀሜታ ሊሰጥ የሚችለውን ትዕይንተ ወግን የሚያህልን መድረክ ልጁ ካለው የጠበበና ያልበሰለ አመለካከት ዓተያይ አስተሳሰብ "ቶክ ሾው አስፈላጊ አለመሆኑንና ጥቅም አልባ መሆኑን ለመግለጽ ነው ዘፈኑን የጻፍኩት" ብሎ ለአንድ የሬዲዮ ዝግጅት ቃለ መጠይቅ በሰጠበት ጊዜ በመግለጹ አስተሳሰቡ ፀረ ዲሞክራሲ (መስፍነ ሕዝብ) እና የደነቆረ መሆኑን ለማስረዳት "ቶክ ሾው (ትዕይንተ-ወግ) ከያኔያንና ጥበብ በሀገራችን!" በሚል ርእስ በጻፍኩት ጽሑፍ ላይ አንስቸው ነበር፡፡

አሁን ደግሞ ይሄው ልጅ በዚያ ሸውራራ ወልካፋ ብዕሩና የድንቁርና ድፍረቱ ኢትዮጵያን የምታክልን ታላቅ ሀገር የሚያጠቃ ድፍረት የተሞላበትና ያስደነገጠኝን ዘፈን ጽፎ በማድመጤ ይሄንን ጽሑፍ እጽፍበት ዘንድ ተገደድኩ፡፡

ጉዳዩ እንዲህ ነው፡- የዘፈኑ ዋነኛ ፅንሰ ሐሳብ "እግዚአብሔር አያዳላም! እውነታው ይሄ ነው" የሚል ሆኖ ኢትዮጵያ ግን "የለም ያዳላል! ለኔ አድልቷል!" ብላ እንዳለች አድርጎ ይቆጥርና እንዲህ በማለቷ ተሳስታለች ብሎ በማሰብ ኢትዮጵያን ለመውቀስ ለመንቀፍ ለማስተማር ለማረም የተጻፈ ዘፈን ነው፡፡ የዘፈኑ ስንኞች እንዲህ ይነበባሉ፡-

ፍርዱ ካያዳላው ፤ ቅን ከሚያይ
ሁሉን ፈጥሮ ፤ ካለው በሰማይ
ከአማልክቶች አምላክ ፤ ከአንድ አባት
ስንተኛ ፍጡር ነን ፤ በእኔ ሞት፡፡
ምሥጢር ለአንቺ ፤ ብቻ የሚልክ
ያዳላልሽ ፤ ሌላን ግን ሲንቅ
አለ ያልሽኝ ቅን አምላክ ፤ ሰማይ
ሁሉን የፈጠረው ፤ ነው ወይ?
ኢትዮጵያዬ ኢትዮጵያ
ጽድቅ እንዲህ ነው ወይ ፤ ንገሪኝ በያ?
ኢትዮጵያዬ ኢትዮጵያ
ጽድቅስ ይህ ነው ወይ ፤ ንገሪኝ በያ?
ማረኝ ስትይ አጥፍተሽ ፤ ጽድቁን ካበራልሽ

ይምረኛል ያልሸው ፤ ልብ የሚራራልሽ
ምን ነው ከሌሎቹስ ፤ ጨክኖ ደበቀ
እውነት ላንቺ ብቻ ፤ በምሥጢር ከላከ
ግልጥ ነው ፤ ባትቀድሚም ሳይቀድሙሽ ፤ ነግሮሻል
በዓለም አያዳላም ፤ ከአፉ ሰምተሻል፡፡
ኢትዮጵያዬ ኢትዮጵያ
አውቃለሁ ይሄን ንገሪኝ በያ**?**
ኢትዮጵያዬ ኢትዮጵያ
ጽድቅ እንዲህ ነው ወይ**?** ፤ ካይደለስ በያ**?**
**-**አዝ**-**
በሥጋ አባቱ ጽድቅ ፤ አጥፊ ልጅ አይጸድቅም
በወላጁም ክፋት ፤ ዘር አይጠየቅም
ጽድቁን ሳታወርስም ፤ እሷው ታመልጣለች
ኃጢአተኛዋ ነፍስ ፤ በእጇ ትቀጣለች
ግልጥ ነው ፤ ባትቀድሚም ሳይቀድሙሽ ፤ ነግሮሻል
በዓለም አያዳላም ፤ ከአፉ ሰምተሻል፡፡
**-**አዝ**-**
የሚል ነው፡፡ እርግጥ ነው እግዚአብሔር አያዳላም፡፡ ይሄ ቃል በቅዱስ ቃሉ ስለተባለ ብቻ ለማለት ያህል የሚባል ሳይሆን እውነት መሆኑን ከልብ ያለጥርጥር ለማመን በሳል ሰው መሆንን ይጠይቃል፡፡ ካልሆነ ግን እግዚአብሔር ያዳላ የሚያስመስሉ ብዙ ነገሮች አሉና የቃሉን እውነትነት ለማመን አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ይህ ቃል እንዲሁ ለሽንገላ የሚጠቀስ ቃል አይደለም፡፡ የገረመኝ **"**ከሌሎቹ የተለየሽ ውብ ድንቅ ልጅ ነሽ**!** የሚደርስብሽ የሚስተካከልሽ የሚያህልሽ የለም**!"** እያለ እንዲያ አድርጎ እግዚአብሔር ስለ ፈጠራት ሴት ከፍ ባለ አድናቆት በጾታዊ ፍቅር እየገለጸ የሚጽፍ ሰው **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** ብሎ ቢጽፍ እየሸነገለ እንጅ ቃሉን ከልቡ አምኖ እየመሰከረ ሊሆን እንደማይችል ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ካልሆነም እዚያው ላይ ጭራሽ ምንም አይሰብም አያምርም የተባለችዋ እንደዚያ የሆነችውና ውብ ድንቅ እያለ እንዳደነቃት ያልሆነችው እግዚአብሔር አድልቶባት ነፍጓት ሳይሆን**...** ስለሆነ ነው ብሎ ሊያሳምናት የሚችልን ቃል ሊነግራት ይገባል፡፡ እንዲያው በደፈናው ግን **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** ብሎ እየተናገረ ዞር ብሎ ደግሞ አንዷን ከሌላኛዋ ለይቶ አልቆ ቢያደንቅ **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** የሚለውን ቃል ከልቡ አምኖ እንዳልተቀበለ ነው የሚያሳየው፡፡ የሚያምንና ይህ ቃል እውነት ነው ብሎ የተቀበለ ሰው አንደኛዋን ከሌላኛዋ ለይቶ ሊያደንቅና ሊወድም ሊንቅና ሊጠላም አይችልም አይገባምም፡፡ በቅጡ ባልተረዳው ነገር በሁሉም ጉዳይ ላይ **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** ብሎ የሚያምን የሚያስብ ሰው በተፈጥሯዊ ገጽታው ሰውን ከሰው ለይቶ ሳያደንቅም ሳይንቅም ሳይወድም ሳይጠላም ሳያማርጥ ለሁሉም እኩል ዋጋ መስጠት መቀበል ይኖርበታል፡፡

እውነቱ ግን ያለው ወዲህ ነው **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** ሲባል ዝም ብሎ በደፈናው **"**አዎ**!** አያዳላም**!"** ተብሎ የሚነገር ቃል አይደለም፡፡ ምን ማለት ነው**?** በምንም ሁኔታ ሁሉ ላይ ነው የማያዳላው**?** ወይስ የሚለዩበት ሁኔታዎች አሉት**?** በምን በምን ጉዳዮች ላይ**?** መቼና እንዴት**?** ብሎ ጉዳዩን አብጠርጥሮ ማወቅ ይጠይቃል፡፡ ይሄንን ሳያደርጉ ልብ ሌላ ነገር እያሰበ በአንደበትም እየተገለጸና ጥያቄዎችን እያነሣ እንዲሁ በደፈናው **"**እግዚአብሔር አያዳላም**!"** ቢሉት አባባሉ እራስን ከመሸንገል የሚያልፍ አይሆንም፡፡




ቃሉ በብዙ ቦታዎች ላይ **"**እግዚአብሔር የሰው ፊትን ዓይቶ አያደላም**!"** ይላል ለምሳሌ ሮሜ**. 2**፥**11** ይህ ማለት **"**ምክንያት ሳይኖረው**"** ለማለት እንጅ አንዱን ከሌላው ለይቶ አብልጦ እንዲያየው እንዲወደው እንዲያከብረው የሚያደርግ የሚያስችል ምክንያት ካለ ግን አያዳላም ማለት አይደለም ግጥም አድርጎ ያዳላል፡፡ እነዚህ እግዚአብሔርን አንዱን ከሌላው ለይቶ እንዲያይ

እንዲያደላ የሚያደርጉት ምክንያቶች በሌሉበት ሁኔታ ብቻ ግን አዎ እግዚአብሔር እኛ እንደምናደርገው ሁሉ ወፍራም ወይም ቀጭን ረጅም ወይም አጭር ቀይ ወይም ጥቁር ቆንጆ ወይም ፉንጋ ወዘተረፈ። እያለ ተፈጥሯዊ በሆነ ነገር ላይ ተመርኩዞ ፈጽሞ ለማንም አያዳላም፡፡ የሰው ፊትን ዓይቶ ለማንም አያዳላም ማለት ይህ ነው ፈጣሪ ነውና፡፡ ሁሉም የሱ የእጁ ሥራዎች ናቸውና፡፡ ስለሆነም "እግዚአብሔር አያደላም!" የሚለው ቃል ሁል ጊዜ በየትም ቦታና በምንም ሁኔታ በምንም ጉዳይ ላይ የሚሠራ አባባል አይደለም ማለት ነው፡፡

እነዚህ እግዚአብሔርን አንዱን ከሌላው ለይቶ እንዲያይ እንዲወድ እንዲያከብር የሚያደርጉት ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? ብለን የጠየቅን እንደሆነ ከመልሱ የነገሩን ቁልፍ ምሥጢር እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔርን አንዱን ከሌላው ለይቶ እንዲወድ እንዲያልቅ እንዲያከብር እንዲባርክ ጸጋና በረከት እንዲሰጥ የሚያደርጉት ምክንያቶች የጽድቅ ሥራዎች ናቸው፣ ፈቃዱን ሕግጋቱን ማክበር መፈጸም ነው፣ መታዘዝ ነው፣ ጽድቁንና መንግሥቱን መሻትና እሱን መምሰል ናቸው፡፡

እንዲህ ስላቹህ ደግሞ ስለ ውበት አንሥተናልና አፍሪካውያን ውበታቸው ቆንጆ ውብ ብለን እንደምናስበው የውበት መለኪያችንን ሚዛን የሚደፉ አይደሉምና ወይም ውብ እንደምንላቸው ሌሎች አለመሆናችንና የቆዳ ቀለማችን መጥቆሩ ጸጉራችን መከርደዱ ወዘተረፈ።

"እግዚአብሔር ስለጠላን ስላደላብን ነዋ!" እንዳትሉ ከቶውንም ምክንያቱ እሱ ስላልሆነ፡፡ ባጭሩ ምክንያቱ ተደጋግሞ እንደተገለጸው የአየር ንብረት ነው፡፡ ባይሆን ኖሮ በሳይንሱም (በመጣቁም) ይሁን በሃይማኖት ሁላችንም የሰው ልጆች ምንጫችን አንድ ዘር ሆኖ እያለ እንዲህ ዓይነት ልዩነት ሊፈጠር ባልቻለም ነበር፡፡ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ እንደ የሃይማኖት ቅዱሳት መጻሕፍት በርካታ ጥቁር ቅዱሳን ያሉ በመሆኑ መጥቆራችን የመረገም ወይም በእግዚአብሔር ከመጠላት የመጣ አይደለም፡፡ ይሄንን የሚል ቃልም የለም! ባጠቃላይ እግዚአብሔር ስላዳላብን አይደለም አካላዊ ገጽታችንን አንዳችንን ውብ አንዳችንን ፉንጋ አንዳችንን አጭር አንዳችንን ረጅም ወዘተረፈ። የሚያደርገን፡፡ ይሄንን ጉዳይ በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን፡፡

ወደ ዋናው ጉዳያችን ስንመለስ ከላይ እንደጠቀስኩት የዘፈኑ ጸሐፊ ኢትዮጵያን "እግዚአብሔር ለእኔ አድልቷል" እንዳለች አድርጎ አስቦ ሲያበቃ እንዲህ በማለቷም የተሳሳተች እንደሆነች ልትታረም እንደሚገባት ሊነግራት ይሞክራል፡፡ ሲጀመር ኢትዮጵያ የዘፈኑ ጸሐፊ በተረዳበት መንገድ "እግዚአብሔር ለእኔ አድልቷል!" አላለችም አትልምም፡፡

ነግር ግን "እግዚአብሔር ከሌላ ለይቶ እንዲያዳላ የሚያደርጉት ጉዳዮች..." ብየ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሁሉ ኢትዮጵያ "እንደፈቃዱ በማደሬ፣ ጽድቁንና መንግሥቱን በመሻቴ፣ ለእሱ የአምላክነቱን ክብርና ምስጋና በመስጠቴ ከሌሎች ለይቶ ወዶኛል፣ አክብሮኛል፣ በጸጋው ጎብኝቶኛል፣ ባርኮኛል!" ትላለች፡፡ "እሱን በመሻቴ ለእኔ አድልቷል" ብላለች ትላለችም፡፡

ቅዱስ ቃሉ "የእስራኤል ልጆች ሆይ! እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላቹህምን? ይላል እግዚአብሔር" ትን። አሞጽ **9፣7** ይላልና፡፡ ይህ ቃል ቀዳሚነቷንም ያረጋግጣል፡፡ የዘፈኑ ጸሐፊ "ከማንም አትቀድሚም" ያለው የተሳሳተ ነው፡፡ ብቻም ሳይሆን ይህ ቃል እግዚአብሔር ላቅ ያለ ፍቅርና ክብር ለእኛ እንዳለውም ያስረዳል ምንም እንኳን ቅጣቱ ባይለየንም ቅሉ፡፡ ቅጣቱም ቢሆን ደግሞ "የጥላቻ ሳይሆን የፍቅሩ መግለጫ ነው፣ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ዲቃላ ነው፡፡ እናንተ ዲቃሎች ሳትሆኑ ልጆች ስለሆናቹህ ነው የምትቀጡት፣ ቅጣቱ የልጅነታቹህ ማረጋገጫና እናንተን የጽድቁ ተካፋዮች እንድትሆኑ ለማድረግ ነው!" ብሎ ቃሉ ተናግሯልና ቅጣቱ ስለበዛ "ስለጠላን ስለተጸየፈን ስለረገመን ነው!" ብለን ልናስብ እንደማይገባ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ዕብ። **12፣5-11** በዚህ ጉዳይ ላይ በዝርዝር ለመረዳት ከፈለጉ "የተባረኩ ሀገራት ወይስ የተረገሙ! የተባረኩ ሕዝቦች ወይስ የተረገሙ!" የሚለውን ጽሑፍ ጎግል አድርገው ያንብቡ፡፡

ሌላው የዚያ ዘፈን ጸሐፊ የተሳሳተው ነገር የዘፈኑ የመጨረሻው ስንኝ ላይ እንዲህ የገለጸው ሐሳብ ነው፡-

በሥጋ አባቱ ጽድቅ ፤ አጥፊ ልጅ አይጸድቅም
በወላጁም ክፋት ፤ ዘር አይጠየቅም
ጽድቁን ሳታወርስም ፤ እሷው ታመልጣለች
ኃጢአተኛዋ ነፍስ ፤ በእጇ ትቀጣለች፡፡

ልጁ ድፍረቱ ይገርመኛል! ስለ ነገረ ሃይማኖት ያለው ግንዛቤ ስንኝ ለመቋጠር የማያበቃ ግልብና ጥራዝ ነጠቅ ሆኖ እያለ ለሕዝብ በሚቀርብና ከባባድ ርእስ ጉዳይ ላይ አንዳች ነገር ሲል ጥቂት እንኳ አይሸማቀቅም አይከብደውም፡፡ ቅዱስ ቃሉ ከታች ከምጠቅሳቸው ጥቅሶች እንደምንረዳው ሁሉም እንደሥራው የሚከፈለው እንደሆነ ቢገልጽም ቅሉ እንደ ሥራችን የሚከፈለን መሆኑን ብቻ አይደለም ቃሉ የሚናገረው፡፡ በአባት ወይም በወላጅ ጥፋት ወይም ኃጢአት ልጅና ትውልዱ የሚቀጣ መሆኑንምና በአባት ወይም በወላጅ ጽድቅ ደግሞ ልጅና ትውልድ የሚጠቀም ምሕረት የሚያገኝ መሆኑንም ጭምር በሚገባ ይናገራል፡፡

"በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና" ዘጸ። **20፣5-6,** "ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል" ሉቃ። **1፣50,** "የእግዚአብሔር ምሕረት ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው፤ ቃል ኪዳኑን በሚጠብቁ ትእዛዙንም ያደርጉአት ዘንድ በሚያስቡ ላይ ነው" መዝ። **102(103) 17-18,** ይላልና፡፡

ክርስቶስስ ከሰው ተወልዶ ወደዚህች ምድር ለመምጣት ታዲያ ምን አስገደደው? የአባታችን የአዳም ኃጢአት በእኛ በዘሩ ላይ ሞት ስላመጣና እኛን ከዚህ እስር ለመፍታት ከዚህ ሞት ለማዳን ለመታደግ አይደለም እንዴ!

ወደ ቀደመው ነገራችን እንመለስና እግዚአብሔር እሱን ላሉት ለታዘዙት ለወደዱት ስለሚያደላም ነው እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና እስራኤልን ከሌሎች ሀገራት ለይቶ፣ ኢትዮጵያዊያንንና እስራኤላዊያንንም ከሌሎች ሕዝቦች ለይቶ ሊወደን፣ ሊያከብረን፣ ከፍ ከፍ ሊያደርገን፣ በቃሉም ሊመሰክርልን፣ ሕዝቤ ልጆቸ እያለ ሊጠራን የቻለው፡፡ ትን። አሞጽ **9፣7,** መዝ። **67(68)፣31,** መዝ። **71(72)፣9,** መዝ። **73(74)፣14,** እንዲህ አድርጎ እንዲያደላልን ያደረገው ነገር ስላለ ነው እሱም ኢትዮጵያ ከመጀመሪያው ጀምሮ እግዚአብሔርን ከማምለክ

እሱን ከመሻት ቦዝና አስተጓጉላ ስለማታውቅ፡፡ በዚህ ድካሟ መሻቷ ጥረቷ ምክንያት ደግሞ ወደዳት፣ አከበራት፣ ባረካት፣ አላቃት፣ በፊቱ ሞገስ ሰጣት፡፡ በቃሉ "ለሁሉ እንደሥራው እንደድካሙ እንደልፋቱ እከፍለው ዘንድ ዋጋው ከእጄ ነው" ብሏልና መዝ. 61(62)፤12, መዝ. 10፤8, 1ኛ ጴጥ. 1፤17፡፡

እናም እንግዲህ አትዮጵያ ከላይ የገለጽናቸውና ሌሎችም ማስረጃዎች አላትና እግዚአብሔር ከሌሎች ለይቶ ስለወደዳት የቃሉ መዝገብ እንዳደረጋት፣ ጸጋ እንደሰጣት፣ የንዋዬ ቅድሳቱ ግምጃ ቤት እንዳደረጋት ብትናገር የዚያ ዘፈን ጸሐፊ እንዴት ነው "ተሳስተሻል ታረሚ!" ብሎ ሊወቅሳት የሚችለው? ነው ወይስ እግዚአብሔርን እንዲህ በማድረጉ "ተሳስተሀል!" ነው ሊል የፈለገው? የልጁ ሐሳብ ደርዝ የሌለው ጥልቀትና ብስለት የራቀው ግልብና ጥራዝ ነጠቅ ነው፡፡ እሱ እራሱ በቅጡ የማያውቀውንና ያልተረዳውን ነገር ግጥም ልጻፍለት ብሎ ጽፎ ለሕዝብ ለማቅረብ ያሰበበት ድፍረቱ ነው የሚገርመኝ፡፡ በተለይ ደግሞ እሱ ራሱ ኢትዮጵያዊ ሆኖ እያለ በዚህ ኢትዮጵያ ባገኘችው የከበረ ስምና ጸጋ ሊደሰት ሲገባው "የሀገር ኩራት የሆነን ስሟን፣ ሀብትና እሴቷን ባልበሰለና በማይሆን ሐሳብ አፍርሽ እንዳይታመን አደርጋለሁ!" ብሎ መጣሩም ሌላው የገረመኝ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህም ምክንያት ደግሞ ልጁ የፕሮቴስታንት (የተቃዋሚዎች) ተከታይ መሆኑ ነው፡፡ እንዴት የሚለውን ዕንይ፡-

ለምን እንደሆነ አይገባኝም ለነገሩ ግልጽ ነው ሌላ ሊሆን አይችልም እሱም የእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ከሚጠላው ከሚዋጋው ካደረባቸው ከክፉው (ከሰይጣን) መንፈስ የተነሣ ነው፡፡ እናም መናፍቃን ለዚህች ሀገረ እግዚአብሔርና ለእሴቶቿ በሙሉ ግራ የሚያጋባና በጣም የሚገርም ስር የሰደደ ጥላቻ አለባቸው፡፡ በየ አዳራሾቻቸው ጠልፈው የሚወስዷቸውን በጎች ተከተታታይ የክህደት ትምህርታቸውን ከመስጠታቸው በፊት የሚከውኑት አንድ ድርጊት አላቸው፡፡ ያንን ሰው እነሱ የሚሉትን ቃል ደግሞ እንዲል እያደረጉ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያንና ኢትዮጵያዊ እሴቶችን በሙሉ እየዘረዘሩ በመርገም እሱም "እርገም" እየተባለ እንዲረግም ያደርጉታን፡፡ ይሄንን እንዲያደርግ ሲያደርጉት ያ ሰው እውስጡ የነበረው የሀገር ፍቅርና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ከውስጡ ተነቅሎ ይጠፋል፡፡ ከዚያም የፈለጉትን የክህደት ትምህርት በእሱ ላይ ለመሙላት ባዶ ምቹና ዝግጁ የሆነ ልብ ወይም ጭንቅላት ያገኛሉ፡፡ በእምነት ስምም የምዕራባዊያንን ጥቅምና ፍላጎትን የማስከበር ግዴታ ያለበት የባንዳነት የሎሌነት የባርነት አገልግሎት ይሞላበታል ይጫንበታል፡፡ የሚገርማቹህ ከዚያ በኋላ እነኝህ ሰዎች "ይሄ የኢትዮጵያ አየር ነው አንተነፍስም!" ማለት ብቻ ነው የሚቀራቸው በሙሉ ኢትዮጵያዊ የሆነውን እሴት ሁሉ ይጠላሉ፡፡

ታዲያ በዚህ መንገድ የተመረዘ መንጋ ኢትዮጵያዊነት ባይሰማው፣ የሀገር ፍቅር ባይኖረው ምን ይገርማል? በቃ! ከዚያ በኋላ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን በተጻራሪ ነው የሚያስቡት የሚቆሙት፡፡ ዘመን አቆጣጠራችንን ሁሉ አይጠቀሙን አዲስ ዓመታችንን አያከብሩም "የኛ አዲስ ዓመት ጃንዋሪ ላይ ነው" ይሏቹሀል፡፡ ሌላው ቀርቶ የባሕል ልብሳችንን እንኳን መጠቀም አይፈልጉም፡፡

ከዓመታት በፊት በዚህ በሚያሳዩት ፀረ ኢትዮጵያዊ እሴቶች ስሜታቸው ላይ በየ ጽሑፎቻና በግጥሞቻቸም ሳይቀር እያነሣሁ አጥብቄ ስወቅስ ቆይቸ ነበር፡፡ በእነዚያ ጽሑፎችና ግጥሞች ከሃይማኖት ውጪ በሆኑ ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን ላይ ያላቸውን ጭፍን አሉታዊ አመለካከት ከንቱነትና ምክንያት አልባነት፤ ከኢትዮጵያዊነታቸው አንጻር ያለባቸውን ግዴታና ኃላፊነት በማሳየት ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ከመቀበል ውጪ ሊያስተባብሉትም ሊሞግቱትም የማይችሉበትን አመክንዮዎችን በማቅረብ ያንን ከንቱ የባርነት የባንዳነት አስተሳሰባቸውን በማጋለጥ ወደ አቅላቸው ወደ ማንነታቸው እንዲመለሱ የሚያስገነዝቡ ነበሩ፡፡ ብዙዎቻቸውንም የጥፋት ሥራቸውን እንዲያስቡ እንዲያውቁ በማድረግ አሸማቀቀ፣ አሳፈረ፣ አሳመነ መሰለኝ በባሕላዊ ልብሶቻችን ላይ የነበራቸው አመለካከት ተለውጦ ከዚያ በፊት እንኳን ሊለብሱት ሊነኩት እንኳን ጨርሶ የማይፈልጉት የነበረው የባሕል ልብሶቻችንን ከዚያ በኋላ ከዕለት ወደ ዕለት በሰፊው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

ለማለት የፈለኩት ከፍ ብየ በጠቀስኩት ምክንያት ነው መናፍቃኑ የሀገር ፍቅር ስሜትና ቁጭት አልባ የሆኑት፣ የባንዳነትና የባርነት ሰብእና ያዳበሩት፣ ዓላማየ ብለውም ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችንን እያጠቁ ያሉት፡፡ ይሄንን የሚያደርጉት ደግሞ በአጋጣሚ ሳይሆን ታስቦበት በአቅድና ዓላማ ነው። በዘፈን ሥራዎች ብቻ ሳይሆን በሁሉም የሥነኪን ሥራዎች ጭምር ለምሳሌ በምትርኢቶች (በፊልሞች) ጭምር ነው፡፡ በዓላማ በመናፍቃኑ ደራስያን እየተደረሱ በየ ቲያትር (ተውኔት) ቤቶችና ፊልም (ምትርኢት) ቤቶች ለዕይታ ከሚበቁት ምትርኢቶች (ፊልሞች) የሚበዙት ጭብጣቸው የፍቅር ወይም ሌላ ጉዳይ ቢሆንም አስታከው ግን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን (ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) ሃይማኖት ያረጀች ያፈጀችና የአሮጊቶች ያልተማሩ ያልሠለጠኑ ሰዎች ሃይማኖት እንደሆነች፤ ፕሮቴስታንትነት (ተቃዋሚነት) ደግሞ ዘመናዊ፣ የተማረ፣ የዚህ ዘመን ሰዎች እንደሆነ በተወከሉ ገጸ ባሕርያትና ድርጊቶች በመንገር ለማሳሳት የሚጥሩ የሚሞክሩ፣ ለሞራል (ለቅስም) ድንጋጌ ትልቅ ዋጋና ቦታ የሚሠጠውን ወግ ባሕልና ሥርዓታችንን የሚያጣጥሉ የሚያንቋሽሹ፣ በዘመናዊነትና በነጻነት ሽፋን ዋልጌነትን ባርነትን የሚመክሩ የሚያበረታቱ የሚሰብኩ ናቸው፡፡ ግራ የሚገባኝና እጅግ የሚገርመኝ ነገር በእነኝህ ምትርኢቶች (ፊልሞች) ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የሆኑ አንጋፋና ወጣት ተዋንያን እየተሳተፉ መተወናቸው ነው፡፡

ሌላው የሚገርመኝ ነገር ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን ደካማ አስተሳሰብ በእነኝህ ድርሰቶች የሚያስገቡ መናፍቃን ደራስያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ "የጥንት ያረጀች ያፈጀች ሃይማኖት" መሆኗን ፕሮቴስታንት ደግሞ "አዲስና የዚህ ዘመን" መሆኑን ካወቁ ይሄ ግንዛቤያቸው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቀደምቷ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታት ትክክለኛዋ መሆኗን፣ ፕሮቴስታንት (ተቃዋሚ) ደግሞ ክርስቶስ በወንጌሉ ማቴ. 24፤1-57 ላይ እንደተናገረው "በኋለኛው ዘመን (በዚህ ዘመን) ይመጣሉ ሐሰተኞች ናቸው" ብሎ የተናገረባቸው እንደሆኑ እንዲገነዘቡ እንዲያውቁ ሊያደርጋቸው ሲገባ ይሄንን መረዳት መገንዘብ አለመቻላቸውና ነገሩን በተገላቢጦሹ መረዳታቸው ነው፡፡

ምክንያቱም ቃሉ ሃይማኖት እንደ ሳይንስ (መጣቅ) አረጀ አፈጀ ተብሎ የሚጣል የሚለወጥ የሚሻሻል የሚታደስ ወይም በአዲስ የሚተካ እንዳልሆነና አንድ ጊዜ ብቻ የተመሠረተ ለሰው ልጆች የተሰጠ መሆኑን ቃሉ አስረግጦ ይናገራልና ነው፡፡ ኤር. 6፤16, ኤፌ. 4፤5, ዕብ. 3፤14, ዕብ. 13፤7-9, ይሁ. 1፤3,

በዚህ ዘመን እንደ አሸን የፈሉት "አዲስና የዘመናዊ የተማረ ሰው" የሚባሉት ደግሞ በአጋንንት የተመሠረቱና ሐሰተኞች የጥፋት መንገዶች

እንደሆኑ በግልጽ ተናግሯልና፡፡ 1ኛ ጢሞ. 4፤1-2, ሮሜ 16፤15-23, 2ኛ ቆሮ. 11፤13

በመሆኑም የእነዚህ ምትርኢቶችና (ፊልሞችና) ሌሎች የሥነኪን ሥራዎች መናፍቃን ደራስያን ይሄንን ግልጽ ግንዛቤ መረዳት ያልቻሉ የማያስተውሉ ለራሳቸው የጨለመባቸው ያላወቁ ያልተማሩ ሆነው ሳለ የያዙትን የተሳሳተ የጥፋትና የክህደት ትምህርት ወይም ግንዛቤ ያለቦታውና ያለ መድረኩ መንገድ እየፈለጉ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በሌላው ላይ ለመጫን ሌላውን ለማሳሳት ለመመረዝ ጥረት የሚያደርጉ ደናቁርት መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ይሄም ልጅ እንግዲህ እንደ ፕሮቴስታንትነቱ (ተቃዋሚነቱ) የዚህ የጥፋት ተልእኮ አራማጅ በመሆኑ ነው ብላሽና ያልገባውን አመክንዮ በመምዘዝ እናት ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያን "እግዚአብሔር አያዳላም ከማንም አትበልጭም አርፈሽ ተቀመጭ፤ ለእኔ አድልቷል እያልሽ አትቀባጥሪ!" በሚል ቅኝት ለመተቸት ለመንቀፍ በመሞከር በዜጎች ልብ ስለ ሀገራችን ያለንን የሀገር ፍቅር ኩራት ስስትና አክብሮት ለመሸርሸርና ለማጥፋት ጥረት ያደረገው፡፡

መናፍቃኑ በያሉበት በየተሰማሩበት መስክ ይሄንን የጥፋት ተግባራቸውን በትጋት እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡ የሚገርማቹህ በአሁኑ ጊዜ ካሉ የዘፈን (የሙዚቃ) አቀናባሪዎች ከጥቂቶቹ በስተቀር በሙሉ መናፍቃን ናቸው፡፡ እነኝህ ግለሰቦች ወደዚህ መስክ ከገቡና የማቀናበሩን ሥራ ከተቆጣጠሩት ወዲህ ያለውን የሀገራችንን ሙዚቃ (ዘፈን) ቃና፣ ጣዕም፣ ዘይቤና ይዘት ብታዩ ከእነሱ በፊት ከነበረው ኢትዮጵያዊ ቅኝት፣ ቃና፣ ጣዕም፣ ይዘትና ዘይቤ የራቀ የተለየ የወጣ ቶሎ የሚሰለችና የሚረሳ፤ መዝሙር እያሉ በየ አዳራሻቸው ከሚያዜሙት የምዕራባዊያኑ ድስ **(touch)** የጎላበት ተጽዕኖው ያየለበት ዜማ ጋር አንድ የሆነ ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም በሀገራዊው የሙዚቃ (የዘፈን) ቃና፣ ቅኝት፣ ጣዕም፣ ይዘትና አሻራ ላይ ምን ያህል ጉዳት እየደረሰ እንደሆነ ባለሞያዎቹ እራሳቸው እንኳን ልብ ያሉት አይመስለኝም፡፡

በዚህ አጋጣሚ በመናፍቃኑ የዜማ ቅኝት ቃናና ዘይቤ ያልተበረዛቹህ ያልተመረዛቹህ የሥነኪን ዝንባሌ ያላቹህ ኢትዮጵያዊያንን ወደ ዜማን ማቀናበሩና ድርሰቱ ላይ እንዲያተኩሩና እየጠፋ እየተበረዘ እየከሰመ ያለውን ኢትዮጵያዊ የዜማ ቅኝት፣ ቃና፣ ጣዕም፣ ወዝ፣ አሻራ ከሞት እንዲታደጉት ማሳሰብ እወዳለው፡፡

እነ አበበ መለሰ እነ አበበ ብርሃኔና ሌሎችም ከእነሱ በፊትም በኋላም ያሉና የነበሩ በባሕል የሙዚቃ ቡድንና በዘመናዊ የሙዚቃ ቡድን የነበሩ አንጋፋ ከያኔያን ይደርሷቸውና ያቀናብሯቸው የነበሯቸው እንዲያ ዘመን አይሽሬ ሆነው የወደድናቸውንና የምንወዳቸውን፣ የሚሸንጡንና የሚመስጡን ጣዕመ ዜማዎች የደረሱልንና የወደድናቸው ከሌላ ከየትም ያመጡት ስለነበረ ሳይሆን ከራሳችን ከሀገር በቀሉ ከእምቅ የጣዕመ ዜማ ሀብታችን የተቀዱ የፈለቁ የራሳችንን የዜማ አሻራ፣ ጣዕም፣ ለዛ፣ ቃና፣ ወዝ፣ ይትበህል የያዙ ስለነበሩና ስለሆኑ፤ የራሳችንን ከራሳችን ለራሳችን ቀድተው ስለሰጡን ነው ጥዑመ ዜማዎቹን እንዲህ ልንወዳቸው ላንረሳቸው የቻልነው ዘመን ተሸጋሪዎች ሊሆኑ የቻሉት፡፡ የመወደዳቸው ምሥጢር ይሄው ነው የኛው ከእኛው ለእኛው ስለሆኑ እኛን እኛን ስለሚሸቱ ነው ሌላ አይደለም፡፡ ይሄ መመለስ አለበት፡፡ ጠፍቶ እንዲቀር በከባዱ እየተሠራበት እንዳለው ደብዛው እንዲጠፋ ፈጽሞ መፍቀድ የለብንም፡፡ በታሪክና በኀሊና ሸንጎ ያስጠይቀናል፡፡

መናፍቃኑ አስቀድመው የቅኝ ግዛት ሰላዮች ሆነው ሰይጣናዊ ዓላማ ሸምቀው እራሳቸው መጡ ከእኛም መጥለፍ የቻሉትን በእምነትና በመሳሰለው ስም ጠለፉና ወሰዱ እነኝህ የተጠለፉት ደግሞ በጥቅሞች በመደለል ራሳቸውን ለባዕዳን ቀጥረው የራሳቸው የሆነውን ሁሉ የሚያጠፉ የባዕዳኑን ጥቅም የሚያስጠብቁና የሚያለሙ ለምዕራባዊያን የባሕል ወረራ ታማኝ ወታደሮች በመሆን ማንነታችንን የሚያፈራርሱ ሊሆኑ ቻሉ፡፡

"በጥቅሞች በመደለል" የምትለዋን ቃል እንደዋዛ እንዳትመለከቷት፡፡ ለመናፍቃኑ (ራሳቸውን ለባዕዳን ቀጥረው በራሳቸው ማንነት ላይ በጥፋት ለዘመቱት) የጥፋት ተግባር ትልቁ ማትጊያ ይህ ነው፡፡ ከፕሮቴስታንቶቹ (ከተቃዋሚዎቹ) ድሀ አባላቶቻቸው አይደለም የምላቹህ ሥራ ቤትና ንብረት ያሏቸው አባላቶቻቸው ሳይቀሩ ልጆቻቸው የሚያድጉላቸው፣ በጥሩ ጥሩ ትምህርት ቤቶች ትምህርት እንዲማሩ የሚደረጉላቸው በምዕራቡ ዓለም ያሉ ተመሳሳይ የእምነት መሰል ተቋም ባሉ አባላቶች ቋሚ ደጋፊነት "ስፖንሰርነት" ነው፡፡ በዚህ መልኩ ልጆቻቸውን ያስተማሩ እያስተማሩ ያሉና ቤት ሳይቀር የሠሩ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ፡፡

እነኝህ ደጋፊዎች (ስፖንሰሮች) በቋሚነት እዚህ ያለውን እንዲያሳድጉና እንዲያስተምሩ የተሰጣቸውን የአንድ መናፍቅ ልጅ በየወሩ በሚልኩት ገንዘብ የማሳደግና የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡ በዚህ መልኩ እየተደገፈ ያደገ ተምሮ ለቁም ነገር የደረሰ ይህ ውለታ ያለበት የመናፍቅ ልጅ ታዲያ በውለታ ታስሯልና እንዲህ በያለበት ተግቶ የተጣለበትን ኢትዮጵያዊ ማንነትን የማጥፋት ዕኩይ ተልዕኮ ተግቶ ቢፈጽም ይገርማል ትላላቹህ?

የሁለቱም ቀጣሪ አንድ ስለሆነ ወያኔም "ድካም አቀለሉልኝ ሥራዬን ሠሩልኝ!" በሚል በዚህ የሚደሰት የበለጠ እንዲያጠፉም ከሕግ ውጪ ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥርላቸው እንጅ የሚከፋ አይደለምና ይሄው በመተባበር በመቀናጀት በማንነታችን ላይ ከዘመቱ ሁለት ዐሥርት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ እንዲህ በመቀናጀት የሚሠሩት ሥራ ማናችንም ከምንገምተው በላይም በአስደንጋጭ ሁኔታ በርካታ ስኬት አስመዝግበዋል፡፡ ወያኔ በሕገ መንግሥቱ ላይ ለአምልኮ ከተፈቀደ ቦታ በስተቀር በመንገድ፣ መጓጓዣ በመጠበቂያ (ፌርማታ)፣ በሥራ ቦታዎች ወዘተረፈ. መስበክ ክልክል ነው ብሎ ቢደነግግም መናፍቃኑ በየመንገዱ ብቻ ሳይሆን ቤት ለቤት ሁሉ እያንኳኩ የክህደት ስብከታቸውን እየሰበኩ ቦነቻችንን ሲነጥቁ ለአንድም ቀን ከልክሎና ሕጋዊ እርምጃ ወስዶ አያውቅም፡፡

ጭራሽም በሀገሪቱ በርካታ ቦታዎች የቀበሌ አዳራሾችንና የግብርና ሚኒስቴር የእህል መጋዘኖችን ሌሎች የመንግሥት ንብረቶች የሆኑ አዳራሾችን ሁሉ ለመናፍቃኑ መስበኪያ እየሰጠ ለዚህ የጥፋት ተልእኳቸው የማያሰልስ ድጋፉን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ አሁንም በሕገ መንግሥቱ የተከለከለውን ማለትም ትምህርት ቤቶችን፣ ጤና ጣቢያዎችን፣ ወፍጮ ቤቶችን ወዘተረፈ. በመደለያነት በማቅረብ ሃይማኖትን ማስቀየር የተከለከለ ቢሆንም አሁንም በዚህ ረገድ ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሳይቀር እንዲስፋፉ አደረገ እንጅ ሕግ ይከለክላል ብሎ ሲገታቸው አልታየም፡፡

በዚህም ምክንያት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም የመናፍቃኑ ቁጥር እጅግ ሊያሻቅብ ችሏል፡፡ በደርግ

ዘመን በ 5% የተወሰኑ ነበሩ፡፡ በዘመነ ወያኔ በተደረጉት ሁለት የኢትዮጵያ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት እንደሚያሳየው ግን የነበሩበትን ቁጥር በእጥፍ በእጥፉ እያሳደጉ መጥተው ባለፈው 1998 ዓ.ም. ቆጠራ 19.5% ስለነበሩ የሬሾው (የአማካኝ) እድገቱ እንደሚጠቁመው ዘንድሮ በሚደረገው ቆጠራ ከ 39% በላይ እንደሚሆኑ ተገምቷል፡፡ ይሄንን ሁሉ መንጋ ከየትም ያገኙት እንዳይመስላቹህ ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የነጠቁት ነው፡፡ በዘንድሮው ቆጠራ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አባላት ቁጥር ደግሞ የእነሱን ግማሽ ከ 15-20% ያህል እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ በየቤቱ ስናየው ወላጆች እንጅ ልጆች ወይም ወጣቶች በመናፍቅነት ወረርሽኝ እንደመበከላቸው ውጤቱ ከዚህ የተለየ እንደማይን መገመት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ወያኔና መናፍቃኑ ከምዕራባዊያን የተሰጣቸው የጋራ የጥፋት ተልዕኮ ስኬት አፋፍ ላይ ደርሷል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ነው አቶ ስብሐት ነጋ “የአማራንና የኦርቶዶክስን አከርካሪ ሰብረናል!” ሲሉ የተናገሩት፡፡

እናም ያለው ነገር ይሄው ነው ኢትዮጵያዊያን ሆይ! እንንቃ ኃላፊነት ይሰማን ማንነታችንን እሴቶቻችንን ቅርሶቻችንን ሀብቶቻችንን በትጋት በንቃት እንጠብቅ በየትኛውም ምክንያት በማንም መጃጃሉ መወናበዱ መታለሉ ይብቃ! ከከባዱ እንቅልፋችን እንንቃ! ወደ ማንነታችን እንመለስ፡፡ የእኛን እግር የሚገጥመውና የሚስማማው የሚመቸው የሚያምርበት የኛ የራሳችን ጫማ እንጅ የባዕዳኑ አይደለም፡፡ እሱ ወይ ይጠበናል ወይ ደግሞ ይሰፋናል፡፡ አያራምደንም አያንቀሳቅሰንም ኧረ ልብ እንግዛ! እናስተውል! እስከ መቸ በራሳችን እንቀልድ? እራሳችንን እያጠፋን በራሳችን ላይ እንዘባበት? እስከ መቸ ሳንበድላቸው ጠላት አድርገው ጥርሳቸውን የነከሱብን ባዕዳን አሽከር ቅጥረኛ ምንደኛ ባንዳ ባሪያ ሆነን መጫወቻና መቀለጃ እንሆናለን?

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

**- See more at: http://www.zehabesha.com/amharic/archives/47618#sthash.0G9D3eaY.dpuf**